የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፵፭
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፫ ቀን ፪ሺ.፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No.45
ADDIS ABABA 21st May, 2020

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፩፻፺፫/፪ሺ.፲፪ ዓ.ም

ለሁለተኛው አገር አቀፍ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ሳኒቴሽንና ሃይጂን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከሳዑዲ የልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ……..ገጽ ፲፪ሺ.፭፻፵፫

## Content

Proclamation No.1193/2020

Saudi Fund For Development Loan Agreement for financing the Second Phase Water Supply, Sanitation and Hygiene Program Ratification Proclamation...........................................Page 12,543

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ.፩፻፺፫/፪ሺ.፲፪

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሳዑዲ የልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ**

ለሁለተኛው አገር አቀፍ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ሳኒቴሽንና ሃይጂን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፪፻፵፫ ሚሊዮን ፯፻፶ ሺህ (ሁለት መቶ አርባ ሦስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ) የሳዑዲ ሪያል የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሳዑዲ የልማት ፈንድ መካከል ታህሳስ ፱ ቀን ፪ሺ.፲፪ ዓ/ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፳፪ ቀን ፪ሺ.፲፪ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### PROCLAMATION NO. 1193/2020

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE SAUDI FUND FOR DEVELOPMENT**

WHEREAS, the Loan Agreement, between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Saudi Fund For Development stipulating that the Saudi Fund For Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 243,750,000 (Two Hundred Forty Three Million Seven Hundred Fifty Thousand) Saudi Riyals for financing the Second Phase Water Supply, Sanitation and Hygiene Program, was signed in Addis Ababa on 19th day of December, 2019;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 30th day of April, 2020;

NOW, THERFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, it is hereby Proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለሁለተኛው አገር አቀፍ የመጠጥ ውሃ አቅርቦት፣ ሳኒቴሽንና ሃይጂን ፕሮግራም ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከሳዑዲ የልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፺፫/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በሳዑዲ የልማት ፈንድ መካከል ታህሳስ ፱ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ/ም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር 8/760 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብ ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብ ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፪፻፵፫ ሚሊዮን ፯፻፶ ሺህ (ሁለት መቶ አርባ ሦስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሃምሳ ሺህ) የሳዑዲ ሪያል በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Saudi Fund For Development Loan Agreement for financing the Second Phase Water Supply, Sanitation and Hygiene Program Ratification Proclamation No. 1193/2020".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement Number 8/760 signed in Addis Ababa on 19th day of December, 2019 between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Saudi Fund For Development is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance</u>**

The Ministry of Finance is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 243,750,000 (Two Hundred Forty Three Million Seven Hundred Fifty Thousand) Saudi Riyals in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the *Federal Negarit Gazettee.*

**Done at Addis Ababa, on this 21st day of May, 2020**

**SAHILEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**